AMHARIC

# ስለ ኮቪድ-19 ክትባት የተለመዱ አሳሳቢ ጉዳዮች

ይህ እስከ መጋቢት 2021 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በጣም ወቅታዊ መረጃ ነው፡ እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ ይዘመናል። ይህ በሐኪሞች የተገመገመ ሲሆን በሕክምናውም ረገድ ትክክለኛ ነው።

## የክትባቱ ሙከራ ደህንነት

የኮቪድ-19 የክትባት ምርምር፡ ከብዙ እና ከተለያዩ ሀገሮች በፍጥነት ብዙ፡ ገንዘብ አግኝቷል። **ክትባቱን ለመስራት የትኞቹም እርምጃዎች አልተዘለሉም።** የኮቪድ-19 የክትባት ሙከራዎች ከ **30,000 እስከ 45,000** ሰዎች ስለነበሩት ብዙ መረጃዎች አሉን።

## ተጓዳኝ ጉዳቶች

**አብዛኛው ሰው የክትባቶቹ ተጓዳኝ ጉዳት አልታየበትም።** አንዳንድ ሰዎች የተከተቡበት ቦታ ላይ ህመም ፣ ድካም ፣ የራስ ምታት ፣ የጡንቻ/የመገጣጠሚያ ህመም ፣ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ የማለት ስሜት ይሰማቸዋል (እንደ ሌሎች ክትባቶች)። በጣም ጥቂት ሰዎች የአለርጂ ምልክቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። **ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳቶች እምብዛም አይደሉም፡ የካናዳ የጤና ጣቢያ፡ ማንኛውንም የረጅም ጊዜ ተጓዳኝ ጉዳቶች መመርመሩን ይቀጥላል።**

## mRNA ከ DNA ጋር ሲወዳደር

**የ Pfizer-BioNTech እና የ Moderna ክትባቶች የእርስዎን DNA አይለውጡትም።** እነዚህ ክትባቶች messenger RNA (mRNA) የተባለ ንጥረ ነገር ይጠቀማሉ። **mRNA** በቫይረሱ ውስጥ የሚገኘውን ፕሮቲን ለመስራት፡ መመሪያ አለው። ይህ ሰውነትዎ፡ antibodies (ፀረ-እንግዳ-አካላት) እንዲሰራ ያስጠነቅቀውዋል፡ ከዚያ ይህን ፕሮቲን ያጠቁ እና ቫይረሱን ይገድሉታል። የተሰሩት ፀረ-እንግዳ-አካላት፡ በሰውነታችን ውስጥ ይቆያሉ፡ **mRNA ው ግን አይቆይም።**

## ማስክ መልበስዎን ይቀጥሉ

**ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ አሁንም ማስክ መልበስ እና ማህበራዊ ርቀትዎን መጠበቅ ያስፈልግዎታል።** ክትባቱን ከወሰዱ በኋላም ቢሆን በኮቪድ-19 የመያዝ ወይም ለሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ ትንሽ እድል አለ።

## እርግዝና እና ህጻናት

**ክትባቶቹ በእርግዝና ላይ ተጽዕኖ አያመጡም።** በክትባቱ የተሠሩ ፀረ-እንግዳ-አካላት: ቫይረሱን እንጂ ሰውነትዎን አያጠቁም። **ይህ በመራባት ላይ ተጽዕኖ እንደማይፈጥር ወይም ለወደፊቱ ፅንስ እንዲወርድብዎ እንደማያደርግ፡** ኮቪድ-19 ከያዛቸው እና ነፍሰ ጡር ከሆኑ ሰዎች፡ መረጃ አለን።

## ማይክሮችፕ የለውም

**ክትባቶቹ በሰውነታችን ውስጥ ቺፕ አያስገቡም።** በክትባቶቹ ውስጥ ጥቃቅን ኮምፒተሮች ፣ ማይክሮ ቺፕስ ወይም የመከታተያ መሳሪያዎች የሉም። **ሰዎችን መከታተል ወይም ክትባቱን ስለወሰደው ሰው የግል መረጃ ማግኘት አይችሉም።**

## ግብዓቶች

በ ክትባቶች ውስጥ ያሉት ንጥረ ነገሮች ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነው - **የደም ምርቶች ፣ ሜርኩሪ ፣ የፅንስ ሴሎች ፣ የአሳማ ሥጋ ፣ የእንስሳት ተዋጽኦዎች ፣ አልሙንየም ወይም ፎርማልድሃይድ የላቸውም።**

## የቀድሞ የኮቪድ-19 ኢንፌክሽን

**በኮቪድ-19 ተለክፈው የነበረ ቢሆንም፡ ክትባቱን መውሰድ ይኖርብዎታል።** በኮቪድ-19 እንደገና ሊያዙ ይችላሉ ምክንያቱም በበሽታው ከተያዙ በኋላ፡ ፀረ-እንግዳ-አካላት በሰውነትዎ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ስለማናውቅ።

ስላነበቡት ነገር እርግጠኛ ካልሆኑ፡ ከሐኪምዎ ወይም ከነርስዎ ጋር ይነጋገሩ።

**እንዲሁም ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፡ የሚከተሉትን የ Public Health ድረ-ገጾች መጎብኘት ይችላሉ፡**

1. https://covid-19.ontario.ca/covid-19-vaccines-ontario
2. https://www.canada.ca/en/public-health/services/diseases/coronavirus-disease-covid-19/vaccines.html

sherbourne HEALTH
REGENT PARK
LOFT
CITY PARK